**ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር __" ደደብማ ባለበት አለ "**

**ጎይታና፡ ትኸሽዎ __ ጎይታይ_ አይከማኹም**

**ከዘርይሁን ሰብሐቱ**

በደርግ ዘመን ነው ፡፡ የአንድ ትልቅ መሥሪያ ቤት ኃላፊ የነበረው እንቶኔ በጥንታዊው የሹም ሽር ሥርዓት እኔ ወደምሠራበት ሚኒስቴር ይዛወራል፡፡ሰውየው በተፈጥሮው ቀዥቃዣና በባኅርዩም ልቅ አንደበት ስለሆነ እንዳንጋጭና ከመጥፎ ደረጃ እንዳንዳረስ ፍርሃት ያዘኝ፡፡ ወዲያው የልብ ጓደኛዬን አገኘሁትና "ተክልዬ - እንደምታውቀው ይኸ ሰውዬ የሰው ክብር የማይጠብቅና እንዳሻው ሰው የሚዘልፍ ነው በቀደም ዕለት አማረን **"ደደብ "** ሲለው በእሱ ምትክ እኔ ስቃጠል ነው የዋልሁት ፡፡ እኔን **"ደደብ"** ካለኝ **"ባለጌ ____ ስዳደግ ! "እብድ"** ነው የምለው አልሁት

በአእምሮ ፍጥነትና በደፋርነት የማደንቀው ጓደኛዬ ወዲያው **"እውነትም ደደብ ነህ**:: እሱ **"ደደብ "** ሲልህ አንተ ለምንድን ነው **"እብድ የምትለው?** ትርፍ ንግግር ውስጥ ሳትገባ **"ደደብ !"** ሲልህ **"ደደብስ አንተ ነህ!** በለው፡፡ ፈራ ካልክ ደግሞ **"ደደብስ ባለበት አለ"** በለው አለኝ ፡፡

ነገሬን እንዳላራዝመው እንጅ እዚያው ከኔ መስሪያ ቤት ባለሙያው ሁሉ የdeadline ውጥረት ስላለበት ጤነኛ ሚኒስትር እንኳ ቢመጣለት አሳብዶ ያባርረዋል እየተባለ ሲወራ ኖሮአል፡፡ታዲያ ባንድ ወቅት ------በ1964-----ከጥላው ጋር የሚጣላ ሚኒስትር ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይመደብልናል ፡፡ ቴሌቪዥኑ በማታ እወጃው ወሬውን እንደ ገለጠልን ዛሬ ስሜን አይጥራውና ወዳጄ መንግስቱ ለማ **(ደራሲው)** ስልክ ይደውልልኝና "ሰማህ ወይ! ከዚህ ቀደም ወደ እናንተ የሚመጣውን ሚንስትር ሁሉ አሳብዳችሁና ጨርቁን አስጥላችሁ የማባረር ዝና

ነበራችሁ አሁን ግን የተጠናቀቀው (ready-made) መጥቶላችኋል” አለኝ፡፡ በእውነቱ ደግሞ ያ ሚኒስትር ጥቂት የማይባሉ ሰዎችን በተራው እንዳሳበደ ተደርጎ ሲወራበት ነበር፡፡

በትህትናና በጨዋነት ተኮትኩቶ ላደገ ሰው “**ደደብ** ” የሚለውም ሆነ “**እብድ**” የሚለው ቅጽል ያስደነግጠዋል፡፡ አንድ ሰው __ለምሳሌ ጌታ መለስ __”**ደደብ** “ቢለኝ ባጠገቤ ሌላ ሰው እንዳለ አማትራለሁ፡፡ ሌላውን ሰው “**ደደብ** ” ማለቱ እንደሆነ በመጠርጠር አለዚያም ተክሌ የመከረኝን መልስ ሰጥቸው የገጸ--ምድር ሕይዎቴ ፍጻሜ ይሆናል፡፡ መቸም በኢትዮጵያ ባሕል ------ያውም በጨዋ ትግርኛ ተናጋሪው ወገናችን ወግ---ላደገ ሰው “**ደደብ** ” የሚለው ቃል ከአፍ ሲወጣ መሸማቀቅ ያለ ነው፡፡ እኔ ከጥፍሬ ውስጥ እገባለሁ፡፡ ሁለተኛ ደግሞ ሰውየው አንድን ማህበረ--ሰብ  አገርና ህዝብ የሚወክል ከሆነ የበለጠ ያስደነግጣል፡፡ ያስፈራል፡፡ የትግራይ ሰው በመልሱና በቋንቋ ምርጫው እጅግ ስለሚጠነቀቅ  እንደ መለስ ያለው የዶሮ --ማነቂያ ልጅ “**ደደብ** ” ቢለው “**አይከማኹም ጎይታይ! ትኸሸዎ ጎይታይ**” ይለዋል፡፡ በዚህም አሥር ሲሲ መርዝ በደሙ ውስጥ ይጨምርበታል!(የትግርኛው ትረጉም በዚህማ እርሰዎን የሚያህል የለም) ማለት ነው፡፡

ተረት---መሰል በሆነ ገለጣ ጀምሬ በዚያው እንዳላስረው እንጅ በዚያ ሰሞን በጨዋታ በጨዋታ አንድ የአዲሱ ዘመን የኢትዮጵያ ጋዜጠኛ የነገረኝን (**ያቀረበልኝን ጥያቄ ላለማለት**) እንቆቅልሽ ላቅምሳችሁ፡፡በጥያቄ መልክ ያጋፈጠኝ እንቆቅልሽ ሌባው እጅግ በለማበት አዲስ አበባ ከተማ ሳይሰበሰብ ከውጭ የሚያድር ምንድን ነው? የሚል ነው፡፡ መልስ ለመስጠት ተወለካከፍሁና “እባክህን የደነዘ ጭንቅላቴን ይቅር በለውና መልሱን ራስህ ንገረኝ” አልሁት “ሳይሰበሰብ ከውጭ የሚያድርማ የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ምላስ ነው” አለኝ፡፡ ይህማ የሰውየው አፍም ክፍቱን እውጭ ያድራል ማለት ነው፡፡ አዎን በጌታዋ የምትተማመን በግ ላቷን ከውጭ ታሳድራለች የሚለው አይነት ነው፡፡ተወቃሽነት፤ተጠያቂነት፤የህሊና ፍርሀት

የሌለበትና በአየረ አየራት ላይ የሚኖርበት ትልቅ ዓለም እስካለው ድረስ "**ሺ.ጊር** " የለም ።
( ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በኂላ አራት ኪሎ ያፈራቸውን ሁለት አምባገነኖችን አሰብሁና ከዚህ ድምዳሜ ላይ ደርሻለሁ። የመጀመርያው ደህናውን መጥቶ አሳብደን አባረርነው። ሁለተኛው ደግሞ ከዶሮ ማነቂያ ሰፈር ተጠናቅቆ መጥቶ ሁላችንንም አባልጎና አሳብዶ ሊጨርሰን ነው )

አቶ መለስ----ወይም ጋዜጠኝነትን ወደ አረሆነት እየወሰዱት ያሉት እነ አይጋና የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን "አንበሳ" እያሉ የሚጠቀሱት " ጠቅላይ ሚንስትር" ከአሥር ቀናት በፊት በሰብአዊ መብት ( ዓለም አቀፍ ) ጉባኤ ላይ የአሜሪካ ዋና ልዑክ የሆነውን ዲፕሎማት " ደደብ " ሲል ተሰምቷል። አመለካከቱና ባሕሉ ከጠፍር የጠነከረ የሆነው ኢትዮጵያዊ አድማጭ ግንባር ላይ ነጭ ላብ ነው የታየው።መለስ ደግሞ ያንን ጋዜጣዊ ጉባዔ ያደረገው (በመሰረቱ) ብርቱካንንና ደጋፊዎችዋን፤ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችንና ሁላችንንም ለመዝለፍ እንደ ሆነ ግልጽ ነበር።በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ አምባገነንቱን፤ዘራፊነቱን፤ነፍሰ ገዳይነቱንና አገር ሻጭነቱን እየተረከ የሚገኙትን ሁሉ ለመዝለፍና ለመሳደብ ብቻ ነው።

ሰሜን ኢትዮጵያን አውቀዋለሁ ስለምል አንዳንድ ሰዎች " ይኽ በትግርኛ እንደ ነውር አይቆጠር እንደሆን " ጠይቀውኛል ። ትግርኛ ተናጋሪ እናቶችና አባቶችማ እንዲህ ያለ ሥርዓትና ለከት የሌለው ቃል ሲሰሙ "አስቀድሞ የሞተ ጸደቀ " ነው የሚሉት ብያቸዋለሁ። ያን ያህል ነው።

ባሻ ወልዴ ሰፈርና ይልቁንም መለስ ብዙ ብዙ የጫራዎች ቋንቋ የተማረበት ዶሮ ማነቂያ ጓደኞቹና ሌሎች ወርበሎች አላፊ አግዳሚው እስኪታዘባቸው ድረስ ማዶ ለማዶ እየተጠራሩ የሚሰዳደቡበት አማርኛ የኢትዮጵያን ባሕል አይወክልም ። የአዲስ አበባ ባሕልም አይባልም።ልባቸው ያበጠ ጥቂት የመቀሌና የአስመራ ጎረምሶች ( ጌታ ኢሳያስ እንዳይቀየሙ እንጅ ) አፋቸውን የሚያላቅቁበትም ትግርኛ የትግራዊውን ኅብረተሰብ ባሕል አያንጸባርቅም።

በጭራሽ ። ስለዚህ በየአደባባዩ ከየወሮበላው የተለቃቀመ አማርኛውን ---ወይም ከጨዋዎች መዝገበ ቃላት እንዲወጣ የተፈረደበትን ይትበሐል በሰማን ቁጥር ልባችን የሚቆም አለን። ያንን በመቀባበል ሰውዬውን አንበሳው መለስ ልክ ልኩን ነገረው------- መለስ አካፋን አካፋ የሚል አንበሳ ነው የሚሉ መጥተዋል። ቀስ በቀስ “ አሸናፊው የይሁዳ አንበሳ !“ ሳይሉት ይቀራሉ ትላላችሁ ( ከዚያ በፊት ግን ስመ---መንግስት ሊያስፈልገው ነው።ዮሐንስ አምስተኛ--አጤ---ምን ይመስላችኋል?)

አንዳንድ የዲያስፖራው ራዲዮ ጣቢያዎች በጀኔቫው የሰብአዊ መብት ዓለም አቀፍ ጉባኤ የአሜሪካ አምባሳደር የሆነውን ልዑክ ለማነጋገር ሳይሞክሩ አልቀሩም። ሰውየው ስለ እኛ በመጠኑ አጥንቶ ምን እንድል ትፈልጋላችሁ? በአገራችሁ “ባለጌን አንድ ጊዜ ስደበው ----- ዘላለም ሲሰደብ -----ይባል የለም ወይ?“ እያለ ነው አለዚያማ  በአገሩ አነጋገር “ደደብ“ የሚለኝ የውሻ ልጅ ማነው እሱ ? ባለ ነበር:: በአሜሪካንኛ  ይኽ ክፋት የለውም።

ከአንዲት የኤሶፐ ተረት ጋር ልለያችሁ።አንድ እረኛ በጎቹን ደህና አሰማርቶ ሲያግጥ ቆይቶ ወደ ምሽቱ ላይ ወደ ቤት ሲወስዳቸው አንዲቱ በግ ከሌሎቹ ፈጠን ፈጠን ብላ ስትሄድ በያዘው ዱላ እግሩዋን ያሰናክለዋል። ስለዚህ በጊቱ እያነከሰች ከጋጡ አጠገብ ስትደርስ እረኛው “ ለጌታዬ እባክሽ አታጋልጭኝ። እሱ ነው የሰበረኝ አትበይ “ ብሎ ይማጸናታል ። የበግ ብልህ የሆነችው ሰባራይቱ እንስሳ ግን “እኔ ባላጋልጥህ ስራህ ይመሰክር የለም ወይ“  አለችው ይለናል የግሪኩ የተረት ሰው።

ከመለስ ጋር ደግሞ የ George  Orwell ን Nineteen-Eighty Four ልተው እፈልጋለሁ ። ድንቁርና በረከት -- እውቀት ደደብነት--ሌብነት ጨዋነት-----ብልግናና ነውር ደፋርነት---ነፍሰ ገዳይነት----ርህራሄ ናቸው። **ትኸሻዎ ኅይታይ! አይከማኹም ኅይታና!**